# ምን አለ፤
# ሕዙብ ምን አለ...

ከሕዝቡ ለሕዝቡ

ቁጥር 1

# መታሰቢያነቱ

መታሰቢያነቱ ለሀገር ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነትና ብልፅግና በያሉበትና በየአቅማቸው አስትዋፅዖ ላደረጉና ለሚያደርጉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይሁን።

# መግቢያ

የሕዝባችንን ጥልቅ ወቅታዊ የፖለቲካ አመለካከት እንዲህ በቀላሉ ተነባቢነት ባላቸውና ለአዕምሮ በሚማርኩ አገላለፆች ማቅረብ ስንጀምር በታላቅ ደስታ ነው።

አስተያየቶችዎንና ተመሳሳይ ስራዎችዎን በሚከተለው e-mail አድራሻችን ይላኩልን።

hagosyabekele@yahoo.com
© 2002 ዓ. ም. እ. ኢትዮ. አ.

*Record with ሃና ሽንቁጤ*

*የዘር ሃረጋችን*

*Sat. May 30 2009* ***በ ሀጎስ ያበቀለ***

# እኔ እና ዜናዊ

በዘሬ - ለሃገሬ
በማንዘሬ - ለድንበሬ
በትውልዴ - አመዴ
ብሔሬ - ጌጤ፤ ክብሬ
ቋንቋዬ - ወግ ማውጊያዬ
በአባቴ - ነኝ ወቴ
በእናቴ - እቴሜይቴ
ሲያረግዙኝ - ወገብ አስያዝኩኝ
ስወጣ - የምጥ ጣጣ
እትብቴ - ነቀምቴ
አገራረዜ - በተከዜ
የወተት ጥርሴ - ለነፍሴ
በስሜ - ጎጃሜ
በልጅነቴ - አዱገነቴ
በትምርቴ - ቄስነቴ
ባነበው - ታሪኬን ነው
ጨርቄ ማቄ - ያው ሰንደቄ
ሃይማኖቴ - ኢትዮጵያዊነቴ
አሟሟቴ - እንዳባቴ
መቃብሬ - ያው ባገሬ

በዘሩ - ለሃገሩ
በማንዘሩ - ለድንበሩ
በትውልዱ - ማበዱ
በብሔሩ - ጠብ መጫሩ
ቋንቋው - ህዝብ መውጊያው
በአባቱ - እንጃባቱ
በናቱ - ቱሪስቱ
ሲያረግዙት - ሊያሶርዱት
ሲወጣ - እንደፌንጣ
እትብቱ - ለድመቱ
በአገራረዙ - ቂም አርገዞ
በወተት ጥርሱ - መናከሱ
በስሙ - አይስማሙ
በልጅነቱ - ማጋጨቱ
ከትምርቱ - ጫካ ቤቱ
ከሚያነበው - የሚዘለው
ጨርቁ ማቁ - መሰንጠቁ
ሃይማኖቱ - መዋሸቱ
አሟሟቱ - የሰው ከንቱ
መቃብሩ - ያው ባገሩ

Record with Filla

Dog eat dog

Sun. May 31 2009 በ ሀጎስ ያበቀለ

# ፍየል ወዲያ

አቦ መለስ - ጥያቄ አለኝ፣
በቀጥታ - መልስልኝ።
አታዟዙር - አታምታታ፣
ቀሚስ ሲሉህ - አትበል ኩታ።
ነጭ ውሸትህ - በኛው ቋንቋ፣
ተስለች - ኧረ ይብቃ።
ከሰሉን ነው - ወተት ያልከው፣
እስኪ ራስህ - አስተውለው።
መሽምጠጡ - ቅጡን አጣ፣
ዘነቆለ - ዓይን አወጣ።

ኧረ - በቃ፣
ሕዝቡ - ነቃ።

ስለ ምርጫው - አልኩህ እኔ፣
ስለ አራምባ - ሕዝብ ውሳኔ፣
ታወራለህ - ስለ ቆቦ፣
ስለ መንገድ - ስለ ቱቦ።
ተፋህኮ - ሽቅብ አሉህ፣
እንደ አክታ - አነቀሩህ።
ደሞም ካልከኝ - ጋዜጠኛ፣
ጥያቄውን - አትስጠኛ።

ኧረ - በቃ፣
ሕዝቡ - ነቃ።

. . .

አታጣመው - እንደ ሽቦ፣
አታሟሟው - እንደ አሻቦ።
ተመዘዘ - እንቶ ፈንቶ፣
አላልቅ አለ - ተጎትቶ።
ሙልጭ ሙልጭ - እንደ አሳ፣
ቁርጥ ቁርጥ - እንደ ቤሳ።
የበሬውስ - ጥጃ መውለድ፣
መቀላመድ - መዘላበድ።
በማር እሰጥ - ማር አገባ፣
ፀሐይ ወጥቶ - ፀሐይ ገባ።

ኧረ - በቃ፣
ሕዝቡ - ነቃ።

እንዲያ ነው ወይ - ያሳደከው፣
እሪያዎቹን - የጠበክከው፣
ወደ ገደል - ሲፏፏጡ፤
አንተ ዐይንህን - ወደ እንጠጠ።
የሰው ማሳ - ሲበሉ አይተህ፣
ቅዝምዝሙን - ተደግፈህ፣
ፊትክን ዞረህ - ወደ ጫካ፣
ሸንት መሸናት - ቅጠሉጋ

ኧረ - በቃ፣
ሕዝቡ - ነቃ።

Record with አስቴር አወቀ

*አሆሆይ ገላ...*　*አመለኛው ቤቴ ፍቅር ነው ማገሩ፣*
*ሰተት ብለህ ግባ ይሽበር መንደሩ።*

*(ከጎፈሬው ፊት ፊት) ይላል ቀና ደፉ፣*
*እንዳልተኛ አረገኝ እንዳላንቀላፉ።*

*በደሳሳ ጎጆ ሃረግ በወረሰው፣*
*ይወጣል ቱባ ልጅ በቅባት የራሰው። ...*

*Sat. May 30 2009* ***በታጋይ በቀለ ተክሉ***

# እንዳበጁሽ

የኛ መተርኮሻ የጥማት ማጥፊያችን፣
የጨካዋ ታጋይ አዜብ ንግሥታችን፣
ለማያውቅሽ ታጠኝ ቦታው ሳልነበሩት፣
እድፈትን ከድንግል ሳይለዩ ለበሉት፣
የኛማ ሙሽራ የኛማ እመቤት፣
በጠኋት መገፋት ሳር ላይ መደፋት፣
በጣይቱ አልጋ ላይ አንሰቶ ኮፈሳት።
　　ጠፍ ጠፍጠፍ ብለሽ ሰርተሽ ለትግላችን፣
　　ጥግብ እርግብ አርገሽ ሁሉን አስገፋሽን።
　　ገና በልጅነት ሲሰራ ታሪክሽ፣
　　ስንት ብዕር ቀለም ቸከቸክንብሽ።
　　ገጾችሽንም ገለጥን በየጣቶቻችን፣
　　እንደዚህ ሳይነትቡ ባለቆቻችን።
　　ለሙጭተሽ ወይበሽ ፈሶ አልቋል መቅኔሽ፣
　　አጥንት አስግጨቸው አሁን ላገኙሽ፣
የቀባንሽ ቅባት ባናትሽ ያረግነው፣
ለንግስሽ መሆኑን ያኔ የት አወቅነው።
እንኳንስ በዶላር እንኳንስ በብር፣
ባንድ ዙርባ ጨትስ ትሰጪ አልነበር።　...

… የወደቀው ጓዴ ለዛ በጎ አላማ፣
አንቺን አነገሰ በኢትዮጵያ እማማ።
እንቁላል ይገማል ብዙ ቀን ሲቆይ፣
የሞተው ጸደቀ ይሄን ጉድ ሳያይ።
አንቺ ምን ታደርጊ ያነሳሽ ጊዜ ነው፣
ክፍት በር ስታይ መግባት ልማድሽ ነው።
ባክሽ ቆለፍ አርጊው ቀንሽ እስኪደርስ፣
ያገር ስም አይጥፋ ስርየት እስኪፈስ።
ሁለተኛዋ አዜብ በረካዋ ማክዳ፣
መዝረፍ የጀመርሽው ስምሽን በማለዳ።
ባፍንጫሽ መጎርጎር ያነባው አይንሽ፣
አሁን አገር ሲሸጥ የት ሄደ ለቅሶሽ።
ለድመት መነኩሴ ያስለመዷት አይለቅ፣
ታስተምሪአለሽ አሉ ኮንዶም አጠላለቅ።
ከወንዶች ላውንቸር ከድብደባው ተርፈሽ፣
ዛሬ የሴቱን መብት ላስጠብቅ ትያለሽ።
ድሮም እንዳበጁሽ እንደምትሰሪ፣
ደሞ እስላም ለመምሰል ታየሽ ስትሞክሪ፣
ሃይማኖት የለሽም ሰው አታሳፍሪ።
የሰማኒያ ባልሽም ያደረ አፋሽ ተኩላ፣
ወንዙንም ሚስቱንም ተካፍሎ እሚበላ።
ጨዋው ኢትዮጵያዊ የተቆነጠጥኩት፣
ይሄን ሁሉ አፍኜ ስንት አመት የኖርኩት፣
ጨዋነት ላገር ነው ብዬ ለወገን፣
አገር ሲጠፋ ሳይ ልናገር ጉድሽን።
ለወልቃይት ወጣት ቡና ቁርስ አዳይዋ፣
ሟጠሽ በያይነቱ የምታደርሺዋ፣
ይሳለቁልሻል በመሸታ ቤት፣
ዘራቸው ዘው ብሎ ከቤተ-መንግሥት።

Record with ሃና ሸንቁጤ

የዘር ሃረጋችን

Sat. December 24, 2009

በ ሀጎስ ያበቀለ

# መለስ ለኢሣያስ

ይድረስ ለኢሣያስ - ለድሮው ወዳጄ፣
የናፍቆት ደብዳቤ - ልፃፍልህ በእጄ፣
አመታት አለፉ - ነገ ዛሬ ስል፣
መምህሬን ሳላገኝ - ልቤ ሲብሰለሰል።
ወንድሜ ሳይመክረኝ - ሳይነደፍ ንድፉ፣
ቀኑ እንዴት ይሮጣል - አይ አስተላለፉ።
እንደቀልድ ተኳርፈን - ምነዋ ቀረን፣
ኧረ ይቅር በለኝ - ጠላት ሳቀብን።

ነብዩ ኢሣያስ - ናፍቆቴ በረታ፣
ባክህ አታክርረው - ያንን ኳስ ጨዋታ፣
የማንነጣጠል - አንድ ሣንቲም ሳለን፣
ዘውድ ነኝ ፣ ጎፈር ነኝ - ብለን ተኳርፈን፣
ትንቢትህ ናፈቀኝ - መሬት ጠብ አይሌው፣
ምድሩን ባሕሩን - የሚሸነሽነው።

በቅዱስ መፅሓፋችን - በተረጎምክልኝ፣
በሚካይል ማክቬሊ - በሰበክልኝ፣
ትራሳችን አርገን - ያኔ ባስጠናኸኝ፣
ባጠመከኝ እምነት - ዕስካሁን ባኖረኝ፣
አንተም ከተንቤን ነህ - እኔም ከአዲቋላ፣
የወንዜ ልጅ ተው ተው - እንዲህ አንጣላ።

...

አሰብን ገብሬ - ባድመን መርቄ፣
ከፍቅራችን ብዛት - ባረኩት አውቄ፣
ወሮታ በከፈልኩ - ላስተማርከኝ ሁሉ፣
ምን ጎድሎብህ ይሆን - ኩርፊያህ መቀጠሉ።

ማስጨኔም ይቀጥል - ቡናውን ጤፉን፣
ብቻ ይቅር ብለህ - እንደ ድሮው እንሁን፣
አንተም በርሃብ ሞትክ - በሞኝ እልህህ፣
እኔም መሄጃ አጣሁ - ደሜን ከፋፍለህ።

እጠብቅሃለሁ - በመልስህ ደብዳቤ፣
ተካፍለን እንብላ - ይረጋጋ ልቤ።

_______________ = _______________

Record with ንዋይ ደበበ

ያ በላይ

Sun. May 31 2009 በሀጎስ ያበቀለ

# ስንተዋወቅ

ጠባችን ካባት ነው ከጥንት ከጠዋት፤
ከደም ካጥንት እንጂ አልመጣም ትናንት።
የአቶ ዜናዊ ልጅ ዛሬ አገር ቢሸጥ፤
አዲስ ነገር ነው ወይ ልብ የሚመስጥ።
ጅብ ሳሩን አይበላ ትቶ አህያውን፤
የባንዳ ልጅ ባንዳ ሌላ ምን ሊሆን።

እኔም የዘሬ ነው ታዲያ ከየት ላምጣው፤
ለወገን መብከንከን ያበሉኝ አላምጠው።
የቁርጥ ቀን ልጆች ከሚበቅሉባት፤
ያ በላይ ዘለቀ ከወደቀባት፤
ከኢትዮጵያ ወገን የወጣሁ ገበሬ፤
ሳር ብቻ እምበላ እየዋልኩ ከበሬ።

ለምዬ ሃገሬ የወረድክ መብረቅ፤
አንተ ሳትጠፋ ከእንቅልፌ አልታረቅ።
የንጨቂ ልጅ ነው ስድቤ ላንተም ይድረስህ፤
ድንበር ቸርቻሪውን በስምህ ልጥራህ።

ልምምጡ ይብቃኝ የነግ የዛሬው፤
በጠር ላነጋግረህ ብጥሊያንኛው።
ካጠፋኸው አይበልጥ ባገር የያዝካቸው፤
ይደር እማትል ጅብ ቀቅለህ ብላቸው።

# በግንቦት

ተመርጦ - ከወራት፣
ለኢትዮጵያ - ግንቦት፣
ብሎ አደለን - እግዜሩ፣
በዚህ ጊዜ - ታሪክ ሥሩ፣
በዚህ ጊዜ - ተነሱ፣
ከሰመረም - ተንፍሱ፣
ካልሰመረም - አልቅሱ።

ያውላችሁ - ፀሐዩ፣
ብርሃኑ - ተስፋ ጣዩ፣
ከሆነም - ለመብራት ነው፣
ካልሆነም - ጠራራ ነው።
ወይ ያበራል - ለሃገር፣
ወይ ያቃጥል - ያሳርር።

አወይ ግንቦት - አይ መባቻ፣
እንዳትበላን - ሰጋሁ ብቻ።
ልክ እንደ አምናው - አነሳስቶ፣
እንዳይበላን - አመካኝቶ፣
ምን ይሻላል - ታሪክ ልስራ፣
ወይስ ይቅር - ሞቴን ልፍራ።
ታመልጥ ይሆን - ይቺ ዕድል፣
ወይስ ትከት - ሕዝቡን ገደል።

…

ምን ይሻላል - አንቺ ግንቦት፣
መቼ ይሆን - ያንቺ ሥምረት።
ሕዝቡ ጓጉቶ - ተነሳስቶ፣
የለውጥ ራዕይ - ፋና ወግቶ፣
ሆ ብሎ - ለሀገሩ፣
ይሆን ብሎ - ለክብሩ፣

እልቂት ይሆን - ዘንድሮም፣
ወይስ ብሥራት - ፍቅር ሰላም።
ታጥቢን ይሆን - በደማችን፣
ይሰበር ይሆን - ቅስማችን፣
ታርጂ ይሆን - ጀግኖችን፣
እናቶችን - ወጣቶችን፣
እስር ይሆን - ውጤታችን፣
ወይስ ሰላም - ላገራችን።

ቀኑ ደርሷል - ምክር ጀባ፣
ያ ፀሎቴም - ያውጣ አበባ፣
ተስፋ አልቆርጥም - ለሃገሬ፣
ልነሳ ነው - ደሞ ዛሬ።

_______________ = _______________

Record with ሃና ሽንቁጤ

የዘር ሃረጋችን

Sat. December 24, 2009

በ ሀጎስ ያበቀለ

# የዘር ተናፅዕሮ (ዘር=$mc^2$)

ሀ ብዬ - በጠኋት፣
ከወንድሜ - መጣላት፣
መጫወቻ - ወሰዶብኝ፣
እያለቀስኩ - ወጣ ካልኩኝ፣
ይከተላል - የሰፈሩ፣
ከእኩያ ጋር - ግርግሩ፣

ና ወንድሜ - አግዝልኝ፣
ጓደኛዬ - ደበደበኝ፣
ብለን ስናልፍ - ሌላ ሰፈር፣
ይከቡናል - በትብብር፣
እኛም መጥራት - ጓደኞችን፣
መከላከል - እንዳቅማችን።

አገር ለቀን - ስንሄድማ፣
የወንዜ ልጅ - የኔ ግርማ፣
ስንባባል - በአንድነት፣
ሲብስብን - መግባባት፣

ፈረንጅ አገር - እንሆንና፣
ሐበሻዊው - ወገኔና፣

...

ማለት አንሶ - በአንድ ቋንቋ፣
ሶማሌውም - 'ኢስት' አፍሪቃ።
ከዚያም አልፎ - በአህጉር፣
መፈላለግ - መፋቀር።

ከቻይናውም - ከሜክሲኮ፣
እየሰፋ - ሲመጣኮ፣
አንተም ያው ነህ - የሩቅ ሰው፣
ስደተኛ - እንደኔው፣
ስንባባል - ስንግባባ፣
በምልክት - በድምፅ አልባ፣

አቤት ሲገርም - የሰው ዘር፣
በንፅዕአሮ - ሲቆጠር፣
ኑሩ ቢባል - ጨረቃ ላይ፣
ወይም በማርስ - ወይ በሰማይ፣
እንል ነበር - ሰው ወገኔ፣
ከምድር ነህ - ና ወደኔ።

ኃያል እኛ - ከፍጥረታት፣
ቀመር ያለን - የብርታት፣
ሕብረት ነበር - አንድነት፣
ለመዋጋት - ለዕድገት።